# ተደራጅ

ጌትነት

ያለ ድርጅት ትግል
ያለ መሥዋዕትነት ድል
ለማምጣት መከጀል
ከንቱ ፊሊጥ መጃጃል
በባዶ ምናብ መዋዠቅ
ከንቱ መመጻደቅ
ይልቅስ ተደራጅ በከንቱ አታቅራራ
ቁጭ ብለህ አታሹፍ ትግሉ ሲጎመራ
ተወው ሃሜታህን
ተወጣ ግዴታህን
መገረፍ መታሰር መታገዝ መገደል
ይብቃ ተነስ ተደራጅተህ ታገል
ከስህተትህ ተማር ድል አይቀርምና
ማጅራት መቺዎች ከቶ አይጠፉምና
እንደ ሕዝባዊ አብዮቱ
እንዳይመታ ማጅራቱ
ሙቀቱ ጨምሯል ቦንቡ ሊፈነዳ
ተደራጅተህ ጠብቅ እንድይሆን ዱብእዳ
እስላም ክርስትያን በጋራ
በአንድነቱ ጎራ
ሕዝባዊ ቁጣውን አሰምቷል
ጠባብ ጎጠኞችን አስደንግጧል
መለስ ፊጦ ሲርበተበት
እንዳጎነበሰ ይሄኔ ነው ማለት
ቦክቶ ሲንቀጠቀጥ
እዚህ እዚያ ሲረግጥ
ብረቱ እንደጋለ መወበዝ መቀጥቀጥ
የሕዝብ ሰይፍ ስሎ ሥልጣን ለማስረገጥ
ተደራጅ ያገር ልጅ እሱ ነው መፍትሔው
ድፈር መሥዋትነት ጠላትክን አጋየው
ተደራጅ ወጥርና ታገል
እንድትበቃ ለድል
ባንዳ ሹምባሹ ይወገዳል
ኢትዮጵያዊነት ያቸንፋል!!